# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 38 መጋቢት 30/2018 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች


የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች በ2018 በጀት ዓመት 9 ወራት የሥራ ክፍሎች ውጤት አመልካች ተግባራት የእቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማዊ ውይይት አካሄዱ

ገጽ 3

ኮሚሽኑ በስልጠና፣ ዲጂታል ሽግግር እና የትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ስራዎችን እያከናወነ ነው - ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ

ገጽ 6

የቻይናውያንን ልብ ያሞቀው የኢትዮጵያውያን የታማኝነት ጥግ

ገጽ 8



የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!


## የዓለምአቀፍ የፀረ-ሙስና ስምምነት አስፈፃሚ የባለድርሻ ተቋማት አመራሮች የአቅም ግንባታ መድረክ ተካሄደ



የመድረኩ ዓላማ የፀረ-ሙስና ስምምነቱ አስፈፃሚ ባለድርሻ ተቋማት በስምምነቱ መነሻ የተዘጋጀው አገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ማስፈጸሚያ ሕጎች፣ ስትራተጂ እና ተቋማዊ አቅም ያለበትን ሁኔታ ለመገምገም ነው:: የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (UN-CAC) በዓለምአቀፍ ደረጃ ብቸኛው የፀረ-ሙስና ሰነድ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም የዚህ ኮንቬንሽን አባል በመሆኗ የሙስና መከላከያ እርምጃዎችን በማጠናከር ዓለምአቀፍ ትብብር ላይ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች:: የዓለምአቀፉ የፀረ-ሙስና ስምምነት አስፈፃሚ ባለድርሻ ተቋማት የሆኑት የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን (የስምምነቱ አገራዊ ተወካይ)፣ፍትህ ሚኒስቴር (የሙስና ወንጀል ክስ የሚመራ)፣ የፌዴራል




ወደ ገጽ 2 የዞረ...


## በመንግስት ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥና ግልጽነት ላይ በተደረገ ጥናት ውይይት ተካሄደ



የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በመንግስት ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥና ግልጽነት ላይ ያጠናውን ጥናት ለዘርፉ አመራሮች አቅርቦ ውይይት ተካሂዶበታል:: ጥናቱ በመንግስት ሆስፒታሎች ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ አሰራሮችን በመለየትና የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማስፈን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው::


ወደ ገጽ 2 የዞረ...


## ኮሚሽኑ ከሰላም ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ዘርፍ ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "የከፍተኛ አመራሩ አርዓያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!" በሚል መሪ ቃል ከሰላም ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ዘርፍ-ተኮር ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል:: ስልጠናዊ ውይይቱ በዘርፉ የሚስተዋሉ ዋና ዋና የሙስና ሥጋት እና ተጋላጭነት መገለጫ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እና ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥና የጥቅም ግጭት ማስተዳደር ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ትኩረት ያደረገ ነው:: በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አቶ መሀመድ ኢድሪስ አመራሮች ውሳኔዎችን ሲወስኑ ምን ያህል የህዝብን ጥቅም አስቀድመናል የሚለውን በማሰብ ከጥቅም ግጭት በጸዳ መልኩ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው ገልጸዋል:: የመንግስት አስተዳደር ባለቤት ህዝብ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ህዝብ የሰጠንን ሀብት ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ እንድናስተዳድር ኃላፊነት አለብን ብለዋል:: ሚኒስትሩ በንግግራቸው አስተሳሰብና አመለካከት ላይ ካልተሰራ ሙስናን በሀብት ማስመለስና በህግ ማስከበር ብቻ መከላከል ያስቸግራል ሲሉ ተናግረዋል:: ውጤት የሚመጣው ነጻ የሆነ የአሰራር ስርዓት ሲገነባ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ስራዎች መርህ ተኮር መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል:: እንዲህ አይነት ስልጠናዊ ውይይቶች የሞራል ልዕልና እንዲኖረንና እራሳችንን ናቸው ብለዋል::

እንድንፈትሽ የሚያደርጉ




ወደ ገጽ2 የዞረ

## ... በመንግስትከገጽ 1 የዞረ



በውይይቱ ንግግር ያደረጉት የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር መቅደስ ዳባ መንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሰፊው እየሰራ መሆኑን ገልጸው፣ በዚህም ወደ ለውጥ ከመጡ ተቋማት አንዱ ጤናው ዘርፍ ነው ብለዋል::

ሚኒስትሯ በንግግራቸው፣ ጥናቱ በጤናው ዘርፍ የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳቦችንና የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ ያግዛል ብለዋል:: የጥናቱ ግኝቶች ለተቋማችን ግብዓቶች ናቸው ያሉት ሚኒስትሯ፣ ብዙ መሰራት ያለባቸውን ጉዳዮች ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎቶቻችንን ከሙስና የፀዳ ማድረግ ይገባናል ሲሉ ተናግረዋል::

በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው በበኩላቸው ኮሚሽኑ ከተሰጠው ተልዕኮዎች አንዱ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት ሙስናን መከላከል ነው፤ይህም ጥናት በመንግስት ሆስፒታሎች አገልግሎት አሰጣጥ ግልጽነት በመፍጠር ለተቋማት ግኝቶችን ማቅረብና ምክረ ሀሳቦችን መስጠት እንደሆነ ገልጸዋል:: የተቋማት ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የሚታገል የሰው ኃይል መገንባት እንደሚገባም አሳስበዋል::

የሰው ልጅ የጤና አገልግሎት ማግኘት መብቱ በመሆኑ የሆስፒታል አገልግሎቶች ከጥቅም ግጭት የፀዱ መሆን አለባቸው፤ ይህንንም አመራሩ በበላይነት መምራት እንዳለበት የገለጹት ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሽኔ ናቸው::

በውይይት ሙስናን ለመከላከል ከሚረዱ መንገዶች አንዱ በጥናት የተደገፉ ስራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ የተጠቆመ ሲሆን፣ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ማስደገፍ እንደሚገባም ተመላክቷል:: ተሳታፊዎች በውይይቱ የተለያዩ ሀሳቦችን አንስተው በተሰጣቸው ምላሽና ማብራሪያ መግባባት ላይ ተደርሷል:: የጥናት ሪፖርቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያጋልጣሉ ያላቸውን 15 የሚሆኑ ግኝቶች ያመላከተ ሲሆን፣ ለእነዚህም የመፍትሔ አቅጣጫዎችን አሰቀምጧል::

በጥናቱ ከታዩና ከተለዩት ክፍተቶች መካከል ለአብነት የታካሚዎች አገልግሎት አሰጣጥ



እንግልት፣ የመድኃኒት አቅርቦትና ስርጭት ለብክነትና ለብልሹ አሠራር መጋለጥ፣ አንድ አንድ የጤና ባለሙያዎች የሥራ ሰዓትን ጠብቆ በሥራ ቦታ አለመገኘትና ዘግይቶ መግባት እንዲሁም ቀድሞ የመውጣት ችግር መታዬት፣ የታካሚዎች የአልጋ አሰጣጥ ግልጽ አሰራርና ስታንዳርድ አለመኖር፣ የህክምና መሳሪያዎችን በአግባቡ አለመያዝና አለመጠበቅ፤ ሲበላሹም በወቅቱ አለማስጠገን እና በሆስፒታሎች የሚሰጡ አገልግሎቶች በስታንዳርድ አለማስተናገድ በጥናቱ ከተስተዋሉ ግኝቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው::

በውይይቱ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር መቅደስ ዳባን ጨምሮ የጤና ዘርፍ ከፍተኛ አመራሮች፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በሥሩ ያሉ የትምህርት ጤና ሆስፒታሎች ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል::

## ... የዓለምአቀፍ ከገጽ 1 የዞረ

ፖሊስ(የሙስና ወንጀል ምርመራና መዝገብ ዝግጅ)፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት (ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር መከላከል) ላይ ሚና ተሰጥቷቸዋል:: እንዲሁም ገንዘብ ሚኒስቴር ፣ ብሔራዊ ባንክ፣ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሚዲያ ተቋማት ጨምሮ 12 ተቋማት ናቸው::በመድረኩ አገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ከማጠናከር አንጻር፣ የባለድርሻ ተቋማት ሰፊ ውይይት አድርገዋል:: እንዲሁም በቆይታቸው በኮንቬንሽኑ አንቀጾች አፈፃፀም፣ መረጃ አሰባሰብ እና የሪፖርት አቀራረብ ስልቶች ላይ ጥልቅ ውይይት አካሂደዋል:: በቀጣይ የፀረሙስና ስምምነቱ አባል አገሮች የአቻ ለአቻ ግምገማ ሥራዎች አስቻይ ሁኔታ የሚፈጠር ይሆናል::

## ... ኮሚሽኑ ከሰላም ከገጽ1 የዞረ



የኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ አመራሩ ቁርጠኛ መሆን እንዳለበት ጠቅሰው፣ መንግስት የህዝብን አደራ ወስዶ እየሰራ በመሆኑ አመራሩ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የህዝብን ጥቅም በማስቀደም መስራት እንደሚገባው ገልጸዋል:: ሚኒስቴሩ ስነ ዜጋ ላይና የህዝብ ንቅናቄ ስራዎች ላይ የሚሰራ በመሆኑ ከኮሚሽኑ ጋር የጋራ ተልዕኮ አለው ያሉት ም/ኮሚሽነሩ፣ በዚህም የትውልድ ሥነምግባር ግንባታን በተቀናጀ መልኩ መስራት አለብን ብለዋል:: በውይይቱ መንግስት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ሙስናን የሚጸየፍ ማህበረሰብ ለመፍጠር በቁርጠኝነት እየሰራ ነው ያሉት ደግሞ የሚኒስቴሩ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ካሳ መንግስቱ ናቸው:: በስልጠናዊ ውይይቱ ስለ ጥቅም ግጭትና ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሰፊ ግንዛቤ እንዳገኙ ተሳታፊዎች የገለጹ ሲሆን፣ በመጨረሻም ጥያቄዎችን፣ አስተያየቶችንና ሀሳቦችን አንስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል::


## በአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በስራ ሰዓት የእጅ ስልክ መጠቀም ተከለከለ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የግብር ከፋዮችን እርካታ ለማረጋገጥና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል በሚያደርገው ጥረት፤ ማንኛውም ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት የእጅ ስልክ መጠቀም የተከለከለ መሆኑን አስታውቋል:: የቢሮውን የአገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመንና በሪፎርም ስራዎች ውጤታማ ለመሆን እየሰራ የሚገኘው የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ፤ በዋና መስሪያ ቤትና በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ከሚገኙ ከ7 ሺህ በላይ ሰራተኞቹ ጋር በስራ ሰዓት ስልክ አጠቃቀም ዙሪያ ሰፊ ውይይት አካሂዷል::

በውይይቱ ላይ እንደተገለጠው፣ ቢሮው የአደረጃጀትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻያዎችን እያደረገ ቢሆንም፤ አሁንም ድረስ ከግብር ከፋዮች ዘንድ የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች እየቀረቡ ይገኛሉ:: በተለይም አገልግሎት ፈላጊን አስቀምጦ በግል የእጅ ስልክ መነካካት እና ለሥራ በተመደበ ኮምፒውተር የግል ጉዳዮችን መከታተል ዋነኛው የአገልግሎት መጓተት ምክንያት መሆኑ ተመልክቷል::

ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ ማንኛውም ሰራተኛ በመደበኛ የስራ ሰዓት የግል የእጅ ስልክ መጠቀም የተከለከለ ሆኗል:: ለሥራ አገልግሎት የተመደቡ ኮምፒውተሮችን ለግል ጉዳይ ማዋል በጥብቅ እንደሚታረም ስምምነት ላይ ተደርሷል:: ሰራተኞች ማንኛውንም ግብር ከፋይ ያለ አድልዎና በቅንነት የማገልገል ግዴታቸውን እንዲወጡ አቅጣጫ ተቀምጧል:: በመድረኩ የተገኙ ሰራተኞች በበኩላቸው፣ ከስልክ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት፤ አሰራሩን ተግባራዊ ለማድረግና ግብር ከፋዩን በታማኝነት ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል::

ይህ አዲስ መመሪያ የመንግስት ተቋማት ተገልጋይን ለማርካት ለሚሰሩት ስራ እንደ ትልቅ ማሳያ የሚወሰድ መሆኑም በውይይቱ ወቅት ተመላክቷል:: የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በሥራ ሰዓት የግል ስልክ መጠቀምን የከለከለው የአገልግሎት መዘግየትን በማስቀረት የግብር ከፋዮችን እርካታ ለማረጋገጥና ለሙስና እንዲሁም ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍቱ ክፍተቶችን ለመድፈን በማለም ነው::



ፀረ – ሙስና

# ኮሚሽኑ ከዘርፍ ፎረም አመራሮች ጋር የስራ ላይ ግምገማዊ ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ዘርፍ በሙስና ሥጋት ጥናት እና በዲጂታል ሀብት ምዝገባ ዙሪያ ያለውን የስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ከዘርፍ ፎርም አመራሮች ጋር ግምገማዊ ውይይት አካሂዷል:: በግምገማዊ ውይይቱ የዘርፍ እንቅስቃሴ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ የኮሚሽኑ የሙስና ስጋት ጥናት ዴስክ ኃላፊዎች አጭር ሪፖርት አቅርበው ውይይት ተካሂዷል:: በዚህ ውይይት አብዛኞቹ ዘርፎች በጥሩ የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሆኑ፣ የተወሰኑ ዘርፎች ላይ ደግሞ ውስንነቶች መኖራውቸን በግምገማው ተመላክቷል:: ውይይቱን የመሩት የዘርፉ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋው እደገለፁት ጥናቱ በቡድን የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን ዘርፎች የጥናት ስራቸውን በየወቅቱ እየገመገሙ እና ክፍተቱን እየሞሉ በተያዘለት ጊዜ ገደብ ጨርሶ ማስረከብ ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል:: የጥናት መረጃው በትክክል ተተንትኖ ግኝቶቹ እና ምክረ ሃሳቦች በትክክል ተዘርዝረው መቅረብ ይኖርባቸዋል ብለዋል::

አያይዘውም በጥሩ የስራ እንቅስቃሴ ወይም ጥሩ አፈጻጸም ላይ ያሉ ዘርፎችን አመስግነው፣ ወደኋላ የቀሩ ዘርፎች ደግሞ ለስራው ትልቅ ትኩረት በመስጠት በአፋጣኝ ጨርሰው ማስረከብ እንዳለባቸው አቅጣጫ አስቀምጠዋል::

የሙስና ሥጋት ጥናት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው በበኩላቸው ይህ ሀገራዊ ጥናት የጋራ ጥረት ድምር ውጤት በመሆኑ ሁላችሁም በሀላፊነት መንፈስ ትኩረት ሰጥጣችሁ መስራት ይኖርባችኋል ብለዋል:: አያይዘውም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ገለልተኛ ሆነው ስራቸውን ማከናወን እንዳለባቸው በመመሪያው ላይ በግልጽ መቀመጡን ገልጸው፣ ነገር ግን በተለያዩ የኮሚቴ ስራዎች በመጠመድ የራሳቸውን ስራ ወደኋላ ማስቀረት እንደሌለባቸው ማሳሰቢያ ሰጥተዋል::

የውይይቱ ሌላው አጀንዳ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ስራ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ የዘርፍ ፎረም ሰብሳቢዎች የየዘርፋቸውን የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ስራ ከእቅዳቸው አንጻር ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ አጭር ሪፖርት አቅርበዋል:: በዚህም ግምገማዊ ውይይት የተወሰኑ ዘርፎች የእቅዳቸውን መቶኛ ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ ዘርፎች ደግሞ የተወሰነ ፐርሰንት ብቻ የቀራቸው መሆኑን እና በአንጻሩም ወደኋላ የቀሩ ዘርፎች መኖራቸው ተመላክቷል::ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክቡር ም/ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው በሰጡት አስተያየት እና ባስተላለፉት መልዕክት እንደ ሀገር 88,000 (ሰማኒያ ስምንት ሺህ) አመራርና ሰራተኞች በዲጅታል ሀብታቸውን ማስመዝገባቸውን እና ውጤቱም የሚበረታታ መሆኑን አስታውሰው፣ ቀሪ ስራዎችም መጠናቀቅ እንዳለባቸው አሳስበዋል:: አያይዘውም በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሀብታቸውን ለማስመዝገብ ፈቃደኛ በማይሆኑ ሰራተኞች ላይ ወደ ቅጣት እንሄዳለን ብለዋል::

የሀብት ምዝገባ ስራ በትኩረት እንዲሰራ የመንግስትም፣ የፓርቲም ጠንካራ አቋም መሆኑን አስረድተው፣ በዚህ ላይ የተቋማት አመራሮች በኃለፊነት እንዲመሩት የዘርፍ ፎረም አመራሮች የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይኖርባችኋል ብለዋል:: እንዲሁም ለማስመዝገብ ፈቃደኛ በማይሆኑ ሰራተኞች ላይ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ኃላፊዎች መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል:: ለዚህም ተግባር የቴክኒክ ድጋፍ ሲያስፈልግ ኮሚሽኑ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋልም ብለዋል::

የሀብት ምዝገባ እና የጥቅም ግጭት መሪ ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ኮኮብ አንበርብር በበኩላቸው የሀብት ምዝገባ ስራውን በዚህ ዓመት በማጠናቀቅ ወደፊት ቀጣይንት ባለው የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት እንሰራለን ሲሉ ገልጸዋል:: ስለሆነም ስራው በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ የፎርም አመራሮች በትኩረት መስራት ይጠበቅባችኋል ሲሉ አሳስበዋል::






# የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የተገልጋዮችን እርካታ በማሳደግ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን እያስቀረ ነው - ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ክብርት ከንቲባ አዳነች አቤቤ 4ኛውን የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍን መርቀው ሥራ አስጀምረዋል:: በዚሁ ወቅት የ'አዲስ መሶብ' የአንድ ማዕከል አገልግሎት የተገልጋዮችን እንግልት በማስቀረት ተጨባጭ ውጤት እያመጣ መሆኑን ገልጸዋል:: በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚሰጡ 240 የአገልግሎት ዓይነቶችም በዲጂታል ሥርዓት እየተሰጡ እንደሚገኙ ተናግረዋል::

የተለያዩ የአገልግሎት ዓይነቶችንም በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በማስገባት ተገልጋዮች ያለአንዳች እንግልት የሚገለገሉበትን ምቹ ምኅዳር መፍጠር እንደተቻለ አንስተዋል:: የ'አዲስ መሶብ' ዲጂታል የአንድ ማዕከልም የህብረተሰቡን የአገልግሎት እርካታ በማሳደግ ሙስና



እና ብልሹ አሰራርን እያስቀረ መሆኑን አስረድተዋል:: በቀጣይም ዜጎች በያሉበት ቦታ ሆነው አገልግሎት የሚያገኙበትን



ተንቀሳቃሽ የ'አዲስ መሶብ' ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል:: በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ቢሮ ኃላፊ ጀማሉ ጀንበር (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አዲስ አበባ በሁሉም መስክ በለውጥ ምህዋር ውስጥ ናት:: በዚህም የ'አዲስ መሶብ' የአንድ ማዕከል አስተማማኝ የኃይልና የኔትወርክ አቅርቦት እንዲኖራቸው በማድረግ የዜጎችን የአገልግሎት ፍላጎት በጥራት እያቀረቡ መሆኑን ገልጸዋል::የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ምስክር ነጋሽ (ዶ/ር)፤ በክፍለ ከተማው ተገንብቶ የተመረቀው የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የታጠቀ ማዕከል ነው ብለዋል::

# የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች በ2018 በጀት ዓመት 9 ወራት የሥራ ክፍሎች ውጤት አመልካች ተግባራት የእቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማዊ ውይይት አካሄዱ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች በ2018 በጀት ዓመት ባለፋት ዘጠኝ ወራት የሥራ ክፍሎች ውጤት አመልካች ተግባራት የእቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማዊ ውይይት አካሂደዋል:: በግምገማዊ ውይይቱ በሙስና መከላከል ዘርፍ፦ የሙስና መከላከል ጥናት፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል እና የሀብት ምዝገባ እና ትክክለኛነት ማጣራት ሥራ ክፍሎች፤ በሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ፦ የፀረ-ሙስና የህዝብ ግንዛቤ ማጎልበቻ፣ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና እና የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ማስተባበሪያ ሥራ ክፍሎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቧል::

በተጨማሪም የዲጂታል ሙስና መረጃ አስተዳደር፣ የፀረ-ሙስና ህጎችና አለምዓቀፍ ሥምምነቶች ማስተባበሪያ እና የተቋማዊ ለውጥ ሥራ ክፍሎች የ2018 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውጤት አመላካች ተግባራት የእቅድ አፈፃፀም ቀርቦ ውይይት ተደርጎባቸዋል::

ከቀረቡ ሪፖርቶች ውስጥ ለከፍተኛ አመራሩ ላይ ትኩረት በማድረግ ስልጠና መሰጠቱ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የሥነምግባር አምሳደሮችን የማፍራት ሥራ መሰራቱ፣ ሀገር አቀፍ የመከታታያ ክፍሎች ትስስር መፈጠሩ፣ በዘርፎች ላይ ችግር ፈች ጥናቶች እየተከናወኑ መሆኑ፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ከአሰራር ወጪ ያሉ ሂደቶችን የማቋረጥ ምጣኔ እያደገ መምጣቱ እና የሀብት ምዝገባ ስራ በዲጂታል ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ በ9 ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በጥንካሬ ተወስደዋል::

እንዲሁም የሙስና መረጃዎች በዲጂታል ሥርዓት ሳይባክኑ ዜጎች በተለያዩ አማራጮች ጥቆማ እያቀረቡ መሆኑና ከባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሠራቱ፤ የዓለምዓቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ሀገራዊ የትስስርና የትበብርር ሥራዎች መጠናከራቸው፤ በአጠቃላይ የተቋምን የአሰራር ሥርዓት ዲጂታላይዝ የማድረግ ስራዎች መሰራታቸው የሚሉት በዋናነት የነበሩ ጥንካሬዎች ናቸው::



በመድረኩ በ9 ወራት የተሰሩ ስራዎች አበረታች እንደሆኑ በተሳታፊዎች የተገለጸ ሲሆን፣ በቀጣይ በክፍተት የታዩ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እቅዶችን ሙሉ በሙሉ መተግበር እንደሚገባ ጠቁመዋል::

በመጨረሻም በሪፖርቱ የታዩ ጠንካራ ጎኖችና ክፍተቶች ላይ ሰፊ ግምገማ የተደረገባቸው ሲሆን፣ በቀጣይ ትኩረት ተደርገው በሚሰሩ ተግባራት ላይም የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች አቅጣጫ አስቀምጠዋል::



## በሥነ-ምግባር ጉድለት ከ400 በላይ ጠበቆች እርምጃ ተወሰደባቸው

በኦሮሚያ ክልል የጥብቅና አገልግሎት ከሚሰጡ ከ1 ሺሕ 900 በላይ ጠበቆች መካከል፤ የሥነ-ምግባር ጉድለት የተገኘባቸው 443 ጠበቆች ላይ እርምጃ መወሰዱን የክልሉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አስታውቋል:: በክልሉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ የለውጥና የሪፎርም ዳይሬክተር አቶ መገርሳ አዱኛ "ከጥብቅና ሥነ-ምግባር ውጭ በሆኑ ተግባራት ላይ ተሰማርተው በተገኙ አካላት ላይ ከአስተዳደራዊ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ሕግ ቅጣት የሚደርስ እርምጃ ተወስዷል" ብለዋል::

በዚህም መሠረት በክልሉ ከሚገኙ 1 ሺሕ 913 ጠበቆች መካከል እስካሁን በ443ቱ ላይ የተለያዩ እርምጃዎች መወሰዳቸው ተገልጿል:: ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን በጠበቆች ላይ ብቻ ሳይሆን፤ መመሪያን መሠረት አድርገው በማይሠሩ ተቋማት ላይም የክትትል ሥራ እንደሚሠራ ዳይሬክተሩ አብራርተዋል:: የሚወጡ መመሪያዎች ተፈጻሚነታቸውን ለማረጋገጥ በተቋማት ላይ ግምገማ እንደሚደረግና መመሪያዎቹን በተግባር በማያውሉ አካላት ላይ ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድም ተናግረዋል::



## ሌብነትና ብልሹ አሰራርን መቀነስ በመቻላችን በከተማችን ተዓምራዊ የሆነ ልማትና እድገትን ማምጣት ተችሏል







ሌብነትና ብልሹ አሰራርን መቀነስ በመቻላችን በከተማችን ተዓምራዊ የሆነ ልማትና እድገትን ማምጣት ተችሏል

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ውይይት አካሄዱ:: የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር መቅደስ ተስፋዬ እንደ ከተማ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን መቀነስ በመቻላችን ተዓምራዊ የሆነ ልማትን እና እድገትን ማምጣት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል:: አገልግሎቶች ፈጣን፣ ቀልጣፋና ከብልሹ አሰራር የጸዱ ሁነው ሲሰጡ የተቋምን ተልዕኮ ለማሳካት አዎንታዊ ፋይዳ እንደሚኖረው ገልጸዋል::

በከተማችን የአገልግሎት አሰጣጡን ውጤታማ ለማድረግ በርካታ ተግባራቶች እየተሰሩ ቢሆንም ከማህበረሰቡ አዳጊ ፍላጎቶች አንጻር የሚቀሩ ነገሮች ስላሉ ሁላችንም ሚናችንን ልንወጣ ይገባል ሲሉ የኮሚሽኑ ፅ/ቤት ኃላፊ አቶ ፈቱ ሰማን አሳስበዋል:: እንደ ኮሚሽን ለውስጥም ሆነ ለውጭ ተገልጋዮች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ፅ/ኃላፊው አመላክተዋል::

የመወያያ ሰነዱን ያቀረቡት የኮሚሽኑ የሰው ሃብት ልማት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ብዙነህ በቀለ ሲሆኑ፣ በየደረጃው በሚሰጡ አገልግሎቶች የሚስተዋሉ ክፍተተችን በፍጥነት ማረምና ማስተካከል ይገባል ብለዋል::

## የዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው - ወ/ሮ ትግስት ሀሚድ



የዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሆኑን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ትግስት ሀሚድ ገልጸዋል:: በዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር ዙሪያ ያሉ ስጋቶችን ለመፈተሽና መረጃ ላይ የተመሠረተ የመፍትሄ አቅጣጫ ለመቀየስ ያለመ ወርክሾፕ እየተካሄደ ይገኛል:: ዋና ዳይሬክተሯ እንደገለጹት፤ የዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል:: ወንጀሉ በፋይናንስ ተቋማት፣ በግለሰቦች፣ በሀገር ኢኮኖሚ እንዲሁም በፖለቲካዊና ማህበራዊ ሥነ-ልቦና ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል ብለዋል::

የዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር በዓለም አቀፍ ደረጃ 5 ትሪሊየን ዶላር የሚደርስ ኪሳራ እንደሚያደርስ ጥናቶች እንደሚያመለክቱም በመጠቆም፤ የዲጂታል ፋይናንስ ማጭበርበር ወንጀሎችን ለመቆጣጠር በጸጥታና ደህንነት አካላት፣ በኢትዮ ቴሌኮም ኦፕሬተሮችና በባንኮች መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር እንደሚገባ አስገንዝዋል:: የወንጀሉን ውስብስብነት በመተንተን፣ የሕግ ክፍተቶችን በመለየትና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ ስልቶችን መንደፍ እንደሚጠበቅም ጨምረው ገልጸዋል:: ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው እና በቸልተኝነት የሚፈጠር ዲጂታል ማጭበርበር በሙስና ወንጀል ስለሚያስጠይቅ እንደዚህ ዓይነት ድርጊቶች ሲኖሩ ሊታረሙ ይገባል ብለዋል::



## ሙስናንና ብልሹ አሠራሮችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያግዝ ስልጠና እየተሠጠ ነው

የሀገርን ሉዓላዊነት የሚጠብቀው የመከላከያ ሠራዊት ሙስናንም ልክ እንደጠላቱ አምርሮ እንዲጠላ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እየተሰጡ መሆኑን የመከላከያ ሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ገልፀዋል:: የመከላከያ ስነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኮሎኔል አዲሱ ሽፈራው ከመከላከያ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቆይታ ከማዕከል ጀምሮ ባሉት አደረጃጀቶች መሠረት ማንኛውንም አይነት የሙስናም ሆነ የብልሹ አሠራሮችን ቀድሞ ለመከላከል የሚያግዝ ስልጠና በተከታታይነት እየተሰጠ ነው ብለዋል::




ለዚህም ይረዳ ዘንድ በዚህ ዓመት ከሁሉም የሠራዊቱ ክፍሎች የተውጣጡ የሥነ-ምግባር መኮንኖችና ሙያተኞች መሰልጠናቸውን አውስተ፣ እነሱ ባገኙት ተደማሪ ዕውቀት የሙስና ፅንሰ ሀሳብ የአመራርና የሙያ ሥነ-ምግባርና ሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሁሉንም የሠራዊት አባላት ተደራሽ ያደረገ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እየተሰጠ ሥለመሆኑ ገልፀዋል::

ከግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በተጨማሪ ለክፍተት የሚዳርጉ አሰራሮችን ማጥናት ማስተካከያ ማቅረብና የተቀመጡ መመሪያዎችና ደንቦች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥም ዳይሬክቶሬቱ የሚከውናቸው ተግባራት ናቸው:: ከሠራተኛው እስከ አመራሩ ሀብትና የገቢ ምንጩን እንዲያሳውቅ በአዋጅ ቁጥር 668/2002 በተደነገገው መሠረት የሀብት ምዝገባ እየተከናወነ ነው ብለዋል ኮሎኔል አዲሱ ሽፈራው::

መከላከያ ለዳይሬክቶሬቱ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ለስራችን ስኬት ድጋፍ ያደርግልናልም ያሉት ዳይሬክተሩ በተቋሙ ውስጥ ካሉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ካላቸው የስራ ትብብር ባለፈ የፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ስልጠናዎችና ሙያዊ ድጋፎችን በመስጠት ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ በመሆኑ አመሥግነዋል::

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

## ርዕሰ -አንቀፅ

# ለፀረሙስና ትግሉ ሚዲያ የማይተካ ሚና አለው!

ሚዲያ በመንግስትና በግሉ ሴክተር ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ የሚሰራ በመሆኑ በፀረ-ሙስና ትግሉ ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ሚዲያ በግልጽነት አለመኖር የሚጎዱ ተቋማትን በመመርመር ለመንግስት እና ለህዝብ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል። በተለይም የምርመራ ጋዜጠኝነት ድብቅ የሙስና ወንጀሎችን ለህዝብ እይታ በማጋለጥ ሙሰኞችን በመዋጋት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ሚዲያ ሚዛናዊ የሙስና መረጃን በማጋራት ግንዛቤ በመፍጠር ህዝብን ያሳውቃል፤ ያነቃልም። በተለየም በምርመራ ጋዜጠኝነት የሚከናወኑ የሚዲያ ሥራዎች ውስብስብና የረቀቁ የሙስና ድርጊቶችን የሙስና ወንጀሎች በማውጣትና በማጋለጥ በመንግስትና በግል ተቋማት ውስጥ የአሰራር ግልጽነት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ሚዲያ የተቋም ኃላፊዎች የተሰጣውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ፣ ተቋማዊ የአሰራር ባህል እንዲጎለብት የመቆጣርና የመግራት አቅም አለው። ከዚህ በተጨማሪ መንግስትና ህዝብ ለአንድ አገራዊ ተልእኮ እነዲሰለፉ፣ ሁለቱን አካለት የማገናኘትና የማስተሳሰር አቅም አለው። የአሰራር ብልሽቶች ከመፈጠራቸው በፊት ህግና ስርዓት እንዲከበር፣ ማህበራዊ ተግባቦት እንዲፈጠር አስቻይ ሁኔታን ይጠቁማል። ሚዲያ በብዙ አገሮች የሙስና ጉዳዮችን በማጋለጥ የህግ ሂደቶችን በማሳየት ተግባራዊ ሚና ይጫውታል።

ሚዲያ በሙስና ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ሊሆን ይችላል። ቀጥተኛ ተፅዕኖዎች ህዝብን ለፀረ-ሙስና ትግል ማነሳሳት፣ ሙሰኞች እንዲቀጡ ማድረግ እና ህጋዊ ምርመራዎችን ማነሳሳት ናቸው። ተዘዋዋሪ ተፅዕኖዎች ደግሞ በህብረተሰብ ውስጥ የተጠያቂነት ባህልን ማጠናከር፣ የፖለቲካ ክርክርን ማበረታታት እና ግልፅነትን ማሳደግ ወዘተ ናቸው። ነገር ግን ይህ ሚና እንዲሳካ ሚዲያው ነፃና ገለልተኛ መሆን አለበት። የመረጃ ነፃነት ህጎች እና ጋዜጠኞችን የሚጠብቁ የህግ መዋቅሮች በዚህ ሂደት አስፈላጊ ናቸው።

ይሁን እንጂ የሚዲያ ባለቤትነት በፖለቲካ ወይም በንግድ ጥቅም ከተገደበ የሚዲያን ነፃነት ሊጎዳ ይችላል። እንዲሁም ጋዜጠኞች በሙስና ጉዳዮች ላይ ሲሰሩ ለአደጋ ሊጋለጡ ይችልሉ። ለምሳሌ በአንዳንዶቹ ማስፈራራት፣ ስደት፣ የግድያ ሙከራና እስር ይፈጸምባቸዋል። ይህ ደግሞ የፀረ-ሙስና ትግሉን ያዳክማል።

ሚዲያ ዜጎችን የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆኑ አዲስ እድሎችን ይፈጥራል። በመሆኑም ዜጎች በፈለጉት የሚዲያ አማራጮች በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እና መረጃን በቀጥታ እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። ሆኖም ግን ከዜጎች የሚመጣው መረጃ ሁሉ በአግባቡ ካልተያዘና ካልተመራ የሀሰት መረጃ ስርጭት፣ ሚዲያ ለህዝብ ያለውን ታማኝነት ሊሸረሽር ስለሚችል በጥንቃቄ መመራት ይኖርበታል። በአጠቃላይ፣ ሚዲያ ሙስናን በመዋጋት ረገድ ወሳኝ መሳሪያ ሲሆን ውጤታማ እንዲሆን ነፃ፣ ገለልተኛ እና ታማኝ መሆኑን መጠበቅ አስፈላጊ ነው።



# ቆይታ

**ኮሚሽኑ በስልጠና፣ ዲጂታል ሽግግር እና ትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ስራዎችን እያከናወነ ነው - የሐረሪ ክልል የሥምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ**



በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ትግል እየጠነከረ በሄደበት ወቅት፣ የክልል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የሚጫወቱት ሚና በጣም ወሳኝ ነው። ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሀገር ልማትን የሚያደናቅፍ፣ የዜጎችን እምነት የሚያጠፋ እና የእድገት ፍጥነትን የሚያዘገይ ትልቅ ችግር ነው። በክልሎች ደረጃም የሚካሄደው ትግል የበለጠ ተጨባጭ እና ቀጥተኛ ከተደረገ ውጤት ማመጣት ይችላል።

በዚህ መንፈስ፣ የሐረሪ ክልል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2018 ዓ.ም በተለያዩ ዘርፎች የተከናወኑትን ተግባራት፣ የተገኙትን ውጤቶች እና ለወደፊቱ ያሉትን እቅዶች በቆይታችን አይተናል። ኮሚሽኑ በዚህ ዓመት ሙስናን ከመከላከል በተጨማሪ ሥነምግባርን በማህበረሰቡ ውስጥ ማጠናከር፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ግልጽነትን ማሳደግ እና ትውልድ በስነምግባር ግንባታ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በተለይ ለሙስና በጣም ተጋላጭ የሆኑ ዘርፎችን በመለየት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በማጠናከር፣ የሀብት ምዝገባን ወደ ዲጂታል ስርዓት በማዞር እና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራዎች ላይ የተገኙትን ስኬቶች አንስተዋል። ከዚህ በታች ክብር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ በቃለ መጠይቁ ያነሷቸውን ዋና ዋና ነጥቦች በዝርዝር እናቀርባለን። መልካም ንባብ!

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ራስዎንና የስራ ድርሻዎትን ለአንባቢዎቻችን ያስተዋውቁልን?

**ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡-** ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ እባላለሁ። በሐረሪ ክልል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሆኜ እያገለገልኩ ነው። ዋናው ተልእኮያችን ሙስናን መከላከል፣ ስነምግባርን በማህበረሰቡ እና በመንግስት ተቋማት ውስጥ መገንባት እና ብልሹ አሰራሮችን በመቀነስ የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥን ማረጋገጥ ነው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በ2018 ዓ.ም በክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምን ምን ተግባራትን አከናውኗል?

**ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡-** በ2018 ዓ.ም ኮሚሽናችን ሙስናን ከመከላከል አንጻር ስልጠና በጣም ትኩረት ሰጥቷል። ስልጠና ሙስናን ለመከላከል ቁልፍ መሳሪያ ስለሆነ፣ ለመንግስት ሰራተኞች እና ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በስፋት ተሰጥቷል። ስልጠናዎቹ በዋናነት አቅም መገንባት፣ ክህሎት ማሳደግ፣ አመለካከት መቅረጽ እና ለሙስና የሚያጋልጡ ክፍተቶችን መዝጋት ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ከዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ የስልጠና ማንዋል፣ ሞጁሎች ማዘጋጀት፣ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እና ጥራትን ማረጋገጥ ተከናውኗል። በዚህ አመት የተሰጡት ስልጠናዎች የተሻለ ውጤት አምጥተዋል ማለት ይቻላል። ስልጠና ብቻ ሳይሆን፣ በጥናት፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል እና የሙስና ወንጀሎችን ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ፖሊስ ኮሚሽን እና ፍርድ ቤት ጋር በመቀናጀት ተግባራትም ተከናውነዋል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በክልሉ ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር በጣም ተጋላጭ ተብለው የተለዩ የመንግስት ተቋማት ወይም ዘርፎች የትኞቹ ናቸው? እነዚህን ክፍተቶች ለመድፈን ኮሚሽኑ ምን ዓይነት ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል?

**ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡-** በክልላችን ለሙስና በጣም ተጋላጭ ተብለው የተለዩት የግንባታ ቢሮዎች፣ መሬት አስተዳደር እና ልማት ኤጀንሲ አካባቢ ያሉ ተቋማት ናቸው። በተለይ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ፍቃድ አሰጣጥ እና ካሳ ክፍያ ጋር ተያይዘው ክፍተቶች ተስተውለዋል። ሁለተኛው ደግሞ የነዳጅ ክትትል እና ስርጭት ዘርፍ ነው። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እንደ ክልል ስትራቴጂካዊ ጥናት በማካሄድ፣ ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ፖሊስ ኮሚሽን እና ፌዴራል ኮሚሽን ጋር በመቀናጀት እየሰራን ነው። ተጋላጭ ዘርፎችን ማዕከል በማድረግ ስልጠናዎችን አጠናክረናል። ከዚህ በተጨማሪም በገቢዎች፣ በመንገድ ትራንስፖርት እና በኢንቨስትመንት ዘርፎች የክፍተት ጥናቶችን በማካሄድ፣ ችግሮችን ለማረም እና ተጠያቂነትን ለማስፈን ስትራቴጂዎችን አውጥተን እንዲተገበሩ እናደርጋለን።

በዘንድሮው ዓመት በፎርጅድ ስራዎች፣ በመንጃ ፍቃድ፣ በሲኦሲ (COC) ስራዎች እና በትምህርት ማስረጃ የሀሰት ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ጥቆማዎችን ተከትለን ምርመራዎች ተጀምረዋል። የመጡ ጥቆማዎችን ወደ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በመላክ ክትትል እናደርጋለን።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የመንግስት ተሿሚዎች እና ሰራተኞች የሀብት ምዝገባ አፈጻጸም በክልሉ ምን ይመስላል? የተመዘገበውን ሀብት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ (Verification) የኮሚሽኑ አሰራር ምን ያህል ውጤታማ ነው?

**ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡-** የሀብት ምዝገባ በክልላችን ወደ ዲጂታል ስርዓት መሸጋገር ዋና አቅጣጫ ነው። በዕቅድ የሀብት ምዝገባ አድሳት 2500 ከታቀደው ከ1500 ገደማ ተግባራዊ ተደርጓል። በቀጣይ ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግ እና ሪፎርም በማካሄድ እየሰራን ነው።

የተመዘገበውን ሀብት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በተለይ በሙስና ተጋላጭ ተቋማት ላይ የጥናት፣ መፈተሻ እና ማጣራት ስራዎችን እያከናወን ነው። መመዝገብ ብቻ ሳይሆን የተመዘገበው ሀብት ምን ያህል ተጋላጭ እንደሆነ በተከታታይ እንከታተላለን። የተመዘገበው ስለትክክለኝነቱ በትኩረት እናረጋግጣለን።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ሙስና ከመከሰቱ በፊት ለመከላከል በማህበረሰቡ ዘንድ የሥነ-ምግባር እሴቶች እንዲሰርጹ ምን ዓይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እየተሰሩ ነው? በተለይ በትምህርት ቤቶች እና በወጣቶች ላይ ያላችሁ ትኩረት ምን ይመስላል?

**ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡-** ዜጎች ከቤተሰብ ጀምሮ ሙያቸውና ስራቸው የሚፈቅደውን ተከትለው እንዲሰሩ ለማድረግ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በስፋት እየሰጠን ነው። በተለይ ትውልድ ስነምግባር ግንባታ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ፣ በትምህርት ቤቶች፣ ተቋማት፣ በገጠርም ሆነ በከተማ የግንዛቤ ስራዎችን እያከናወን ነው።

በቴክኒክና ሙያ፣ መሰናዶ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 36 የስነምግባር አምባሳዶሮች በስነምግባር አርዓነት ያላቸውን በመምረጥ ተልእኮ ሰጥተን እያሰማራናቸው ነው። ሌሎች ተማሪዎችም የአምባሳደሮችን አርዓያነት ለመከተል የሚያደርጉት ጥረትና መነቃቃት በጣም አበረታች ነው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በዲጂታል ሀብት ምዝገባ እና በዲጂታል ጥቆማ ስርዓት ምን ዓይነት ስራዎች ተሰርተዋል? ኮሚሽኑ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ ምን ሰርቷል?

ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡- የሀብት ምዝገባን ወደ ቴክኖሎጂ(በዲጅታል ሀብት ምዝገባ) በማዞር ዜጎች በቀላሉ እንዲጠቀሙ አድርገናል። በዲጂታል ጥቆማ ስርዓትም ዜጎች ጥቆማ እንዲሰጡ ግብዓቶችን እያሟላን ነው። ከኢኖቬሽን አገልግሎት ጋር በመተባበር በቅርቡ ሙሉ በሙሉ ቴክኖሎጂውን ለመተግበር እየተዘጋጀን ነው። እነዚህ የቴክኖሎጅ ውጤቶች ለምተው ወደ ስራ እስኪገቡ በተለያዩ ዘዴዎች በሚቀርቡ ጥቆማዎች መሰረት መመለስ ያለባቸውን ሀብቶች እያስመለስን እና መታረም ያለባቸውን የአሰራር ክፍተቶች በፍጥነት እንዲታረሙ እያደረግን ነው።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** መጨረሻ ማለት የሚፈልጉት ካለ?

ክቡር ኮሚሽነር አዳል ሙላቱ፡- ሙስና የሁላችንም አጀንዳ ነው። ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የተጀመረውን መነቃቃት በቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ትውልድ ሥነምግባር በመገንባት እና ግንዛቤ በመፍጠር ሁሉም ባለድርሻ አካላት (ሚዲያዎች፣ ዜጎች፣ ተቋማት) በጋራ መሳተፍ ይገባል። ኮሚሽኑ መሪነትን ይወስዳል፣ ነገር ግን ዘላቂ ውጤት የሚመጣው በጋራ ትብብር እና ተጠያቂነት ብቻ ነው።

እናመሰግናለን!

# ሳይቃጠል በቅጠል

## ኮሚሽኑ ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚፈጥረው ትብብር ለሙስና መከላከል ያለው ፋይዳ ወሳኝ ነው!



ኮሚሽኑ ከአለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚፈጥረው ትብብር ለሙስና መከላከል ያለው ፋይዳ በጣም ትልቅ ነው። የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ብቻውን ሙስናን ማሸነፍ እንደማይችል በመገንዘብ፣ ከብሔራዊ፣ ክልላዊ እና አለም አቀፍ አጋሮች ጋር ያለውን ትብብር እንደ ስልታዊ መሳሪያ ይጠቀማል። ይህ ትብብር የቴክኖሎጂ፣ የህግ፣ የመረጃ ልውውጥ እና የአቅም ግንባታ ጉዳዮችን ያጠናክራል።

ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 1236/2021 (የተሻሻለው የፌዴራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ) መሰረት ከአለም አቀፍ እና አህጉራዊ ተቋማት ጋር ትብብር ለማድረግ፣ ሀገሪቱን በፀረ-ሙስና ጉዳይ በብቃት ለመወከል ህጋዊ ስልጣን ተሰጥቶታል። ይህ ስልጣን የመረጃ ልውውጥ፣ የሙስና ጉዳዮችን ማስተባበር እና የቴክኒክ እርዳታ ጉዳዮችን ይጨምራል።

የተባበሩት መንግስታት የእጽ እና ወንጀል ቢሮ (UNODC) ኮሚሽኑ ከUNODC ጋር በትብብር ይሰራል። የጋራ ስራዎች የቢዝነስ ኢንተግሪቲ (የንግድ ስነምግባር) ፖሊሲ ማዘጋጀት፣ የኢትዮጵያ UNCAC (የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን) ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች (ዲጂታል ፎረንሲክስ፣ ፋይናንሻል ምርመራ) እና አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን ያከብራሉ። የዓለም ባንክ StAR Initiative (Stolen Asset Recovery) የተመዘበረ ሀብትን ለመከታተልና ለመመለስ ይተባበራል። የኢንተርናሽናል የፀረ-ሙስና አካዳሚ (IACA) የመግባቢያ ስምምነት (MoU) ተፈርሟል። ይህ ስምምነት የጋራ ስልጠና፣ የመረጃ ልውውጥ እና የፀረ-ሙስና ትምህርት ፕሮግራሞችን በጋራ መስራትን ያካትታል።

ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ ፀረ-ሙስና ባለስልጣናት ማህበር (EAAACA) አባል ሀገር ስትሆን፣ የፌዴራል ስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኑ ብዙ ጊዜ ጉባኤዎችን አስተናግዷል (ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከአሁን በፊት ጉባኤ ተካሂዷል)። ማህበሩ በዋና ዘርፎች ማለትም የቀጠናዊ ሀብት ማስመለስ፣ የመረጃ ልውውጥ፣ የጋራ ምርጥ ልምዶች ማካፈል እና ARIN-EA (Asset Recovery Inter-Agency Network for Eastern Africa) በኩል ቀጥታ ትብብር ያደርጋል። ሌላው ደግሞ የምስራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግስታት ባለስልጣ(IGAD) (Inter-Governmental Authority on Development) ኢትዮጵያ የIGAD ኮንቬንሽን ላይ ተፈራርማለች። ይህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ህጋዊ ትብብሮች(Mutual Legal Assistance (MLA)) እና የሙስና ወንጀል የፈጸሙ ተጠርጣሪዎችን አሳልፎ መስጠት (extradition) ጉዳዮች ላይ ይተባበራል።

ይህ ትብብር ለሙስና መከላከል የሚሰጠው ፋይዳ በሚከተሉት መልኩ ይታያል። ድንበር ተሻጋሪ ሙስናን መከላከል በEAAACA እና IGAD በኩል መረጃ መለዋወጥ እና ተከሳሾችን አሳልፎ መስጠት ይቻላል። ሙስና ብዙውን ጊዜ ድንበር ተሻጋሪ በመሆኑ፣ ይህ ትብብር በጣም ወሳኝ ነው። ሀብት ማስመለስ (Asset Recovery) በUNODC፣ StAR እና ARIN-EA በኩል በውጭ የተደበቀ ሀብት ለመከታተል እና ለመመለስ ጠንካራ ማዕቀፍ ተፈጥሯል። በ2017ዓ.ም በፓርላማ የጸደቀው የንብረት ማስመለስ አዋጅ ቁጥር 1364/2017 ይህንን ትግል በከፍተኛ ደረጃ ያጠናክራል። ሙሰኞች <<ሰርቀን የሰረቅነውን ሀብት እንበላለን>> የሚሉትን እሳቤ የሚሰብር እና መመለስን የሚያስችል አዋጅ ነው።

አቅም ግንባታ (Capacity Building) የUNODC እና IACA ስልጠናዎች የኮሚሽኑ ባለሙያዎችን በዲጂታል ፎረንሲክስ፣ በፋይናንሻል ምርመራ እና በሌሎች ዘመናዊ ቴክኒኮች ያጠናክራሉ። የሀገር ገጽታ ማሻሻል ከእነዚህ ተቋማት ጋር ያለው ትብብር የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት ለመሳብ እና የብድር መጠንን ለማሻሻል፣ የተቋማትን አቅም ለማጠናከር እና ለፍትሕ መስፈን ትልቅ አስተዋጽኦ ያበርክታል። ይህ በተለይ የኢኮኖሚ እድገትን በጉልህ ያበረታታል።

ሙስና ድንበር ተሻጋሪ የሆነ፣ ውስብስብ እና በቴክኖሎጂ የተቀናጀ ችግር ስለሆነ፣ የአለም አቀፋዊ ትብብር መፍጠር ሙስናን በመከላከል ረገድ ያለው ፋይዳ የማይተካ ነው። በአጠቃላይ፣ ይህ ትብብር የኢትዮጵያን የፀረ-ሙስና ትግልን ያጠናክራል፣ የተቋማትን ብቃት ያሳድጋል፣ የተመዘበረን ሀብትን ለማስመለስ ያግዛል፣ ለተመጣጣኝ ልማትና ፍትሕን ለማስፈን ትልቅ አስተዋጽኦ ያበርክታል። ስለሆነም ትብብሩን የበለጠ ማጠናከር ውጤታማ ያደርጋል።

## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረውን የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት ሲሆን፤ ሀገራችን ከሙስና ወንጀል ጋር ተያይዞ ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ በኮሚሽኑ፣ በፖሊስና አቃበ ህግ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው::

በመሆኑም ፊንቴክ ኢንቬስትመንት የግል ድርጅት መስራችና ባለቤቶች የሆኑት ዳንኤል ዮሃንስ ኢየሱስ እና ግርማይ ገ/ሚካኤል ይህደጎ የተባሉት ተጠርጣሪዎች ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን በመጠቀም ከ1,200 በላይ ዜጎችን በማጭበርበር የ1.7 ቢሊዮን ብር ጉዳት በማድረሳቸው በ19 ዓይነት የተለያዩ ወንጀሎች ምርመራ አጣርቶባቸው ለዐቃቤ ሕግ በመላክ ዓቃቤ ሕግ ክስ መመስረቱን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ አስታውቋል:: መጀመሪያ ክሱ የቀረበው ለአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ቢሆንም ምርመራው ውስብስብና ከፍተኛ ልምድ የሚጠይቅ ድንበር ተሻጋሪ በመሆኑ በተደራጀ መልኩ መጣራት ስላለበት ጉዳዩን ወደ ኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ በማምጣት ምርመራው በስፋት ሲጣራ መቆየቱ ተገልጿል::

ተጠርጣሪ ዳንኤል ዮሃንስ ላይ ክስ ተመስርቶበት ማረሚያ ቤት ሆኖ ክሱን እንዲከታተል መደረጉንና ተጠርጣሪ ግርማይ ገ/ሚካኤልን ደግሞ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ክትትል እያደረገ መሆኑን የገለፀው የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ግርማይ ገ/ሚካኤል የተባለው ግለሰብ ከዚህ ቀደም እ.ኤ.አ አቆጣጠር በ2,010 የደቡብ አፍሪካ የዓለም የእግር ኳስ ሻምፒዮና ወቅት አስካሉካን በተባለ ድርጅት ስም ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄዳችሁ የዓለም ዋንጫ እንድትመለከቱ አደርጋለሁ በማለት ዜጎችን አጭበርብሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ካሰባሰበ በኋላ ተደብቆ ከሀገር በመውጣቱ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ከኢንተርፖል ጋር በመተባበር ባደረገው ጠንካራ ክትትል ከተደበቀበት ሀገር ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ አድርጎ በሕግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆን ማድረጉን የወንጀል ሪከርዱ እንደሚያመላክት አስረድቷል::

ሁለቱ ተጠርጣሪዎች ተጎጂዎችን 50% ቅድመ ክፍያ 950 ሺህ ብር በማስከፈል በ90 ቀናት ውስጥ የመኪና ባለቤት እንደሚያደርጓቸውና ቀሪ 950 ሺህ ብር ደግሞ ያለወለድ በ5 ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ የባንክ ብድር እንደሚያመቻቹላቸው በመግለጽ ዜጎችን በማጭበርበር ክፍያውን እንዲፈጽሙ አድርገዋል ሲል የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ገልጿል:: ተጠርጣሪዎቹ ኅብረተሰቡን ለማሳመን 148 መኪኖች ከጅቡቲ በማስገባት 100 መኪኖች ለተወሰኑ ግለሰቦች እንዲከፋፈል በማድረግ እና ቀሪ 48 ዘመናዊ መኪኖችን መርጠው በድብቅ መሸጣቸውን እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ስለመግባታቸው ምንም አይነት መረጃና ማስረጃ ሳይኖር 350 መኪኖችን ከውጭ እንዳስገቡ በማስመሰል ኅብረተሰቡን ሲያጭበረብሩ እንደነበር ፖሊስ በምርመራው አረጋግጧል::

በተጨማሪም በጅቡቲ ወደብ ምንም ዓይነት መኪና ሳይኖር 400 መኪኖች ጅቡቲ ወደብ ላይ እንደቆሙና ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት በሂደት ላይ እንዳሉ በማስመሰል ለተጎጂዎች ሐሰተኛ መረጃ



መስጠታቸውን ፖሊስ ማረጋገጥ ችሏል:: በመስቀል አደባባይ ከተለያዩ ቦታዎች መኪኖችን በትውስት በማሰባሰብ ሕዝብን በሚያሳስት መልኩ ድርጅቱ ከውጭ ሀገር ያስገባቸው መኪኖች እንደሆኑ በማስመሰል እና የኤሌክትሪክ መኪና አምራች ከሆነው BYD ከተባለ የቻይና ካምፓኒ ጋር ምንም ዓይነት ውል ሳይኖራቸው ውል እንዳላቸው አድርገው የማጭበርበር ወንጀል ሲፈጽሙ መቆየታቸውን ፖሊስ በምርመራ ደርሼበታለሁ ብሏል::

ተጠርጣሪዎቹ በጅቡቲ ውስጥ አልፋቲዞ በሚል ስም ድርጅት በማቋቋም BYD ከተባለ የቻይና ካምፓኒ ጋር አብሮ ከሚሰራ ሌላ ድርጅት ጋር በመነጋገር 10% ቅድመ ክፍያ በመክፈል የመጀመሪያዎቹን 148 መኪኖች ወደ ሀገር ውስጥ አስገብተው እንደነበርና ተጨማሪ 188 መኪኖችን በተመሳሳይ 10% ቅድመ ክፍያ ለድርጅቱ በመክፈል መኪኖቹን ተረክበው ወደ ሀገር ውስጥ ሳያስገቡ ጅቡቲ ላይ እንዲሸጡ ማድረጋቸውንና በአጠቃላይ 336 መኪኖችን 10% ጅቡቲ ለሚገኘው የቻይና ድርጀት በመክፈል ወስደው ቀሪ 90% ክፍያ አለመፈፀማቸውን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ባደረገው ምርመራ ደርሶበታል::ከ1,200 በላይ ተጎጅዎችን በማጭበርበር መዝግበው 95 ሺህ ብር ቅድመ ክፍያ፤ 285 ሺህ ብር የመንግስት ታክስ እንዲሁም 130 ሺህ ብር ለኤክትሪክ መኪና ቻርጀር ለማሰራትና ለባለሙያ በሚል ከእያንዳንዳቸው 1 ሚሊየን 365 ሺህ ብር መቀበላቸውን ፖሊስ አረጋግጧል::የፊንቴክ ኢንቨስትመንት ድርጅትን ባልተገባና በተጋነነ መልኩ በማስተዋወቅ በህገወጥ መንገድ ከተሰበሰበው ገንዘብ ተጋሪ በመሆን የተጠረጠሩ ሰለሞን ቦጋለ፣ ሰራዊት ፍቅሬ፣ ዳንኤል ተገኝ፣ አብርሃም ግዛው፣ ይገረም ደጀኔ፣ መንሱር ጀማል እና ካሊድ ናስር የተባሉ ታዋቂ አርቲስቶችና የማስታወቂያ ባለሙያዎችንም የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ በቁጥጥር ሥር አውሎ ፍርድቤት በማቅረብ የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆባቸው ፍርድ ቤትም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2018 ዓ.ም መፍቀዱ ተገልጿል::

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ በማጭበርበርና በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብ (Money laundering) እና የድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ጨምሮ በ19 የወንጀል ጉዳዮች በተጠረጠሩ የፊንቴክ ኢንቬስትመንት ድርጅት መስራቾችና ባለቤቶች እንዲሁም በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸዉን ዕውቅናና ተቀባይነት በመጠቀም ሆን ብለው የተጋነነ ማስታወቂያ በመንገር እና በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያ የሀሰት መረጃዎችን ለህብረተሰቡ በማሰራጨት ዜጎችን እንዲጭበረበሩ በማድረግ በሕገወጥ መንገድ ከተገኘዉ ገንዘብ እያንዳንዳቸዉ አሁን ባለዉ የገበያ ዋጋ ስምንት ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ቢ..ዋይ.ዲ ሶንግ ፕላስ የመኪና ስጦታ በመቀበል፤ በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብ (Money laundering) እና በዜጎች ላይ ከ1.7 ቢሊየን ብር በላይ ጉዳት በማድረስ በተጠረጠሩ አርቲስቶችና የማስታወቂያ ባለሙያዎች ላይ የጀመረውን ምርመራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል::

## መልካም ዜጋ

### የቻይናውያንን ልብ ያሞቀው የኢትዮጵያውያን የታማኝነት ጥግ

ከብር በላይ "ታማኝነት" በብሔራዊ ሙዚየም የተገኘው የሥነ-ምግባር አርዓያ! ሶንግ ጀንግ የተባለ ቻይናዊ ጎብኝ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ የኢትዮጵያን የጥንት ታሪክና ባህል ለማየት የካቲት 7 ቀን 2018 ዓ.ም ወደ ብሔራዊ ሙዚየም አመራ:: ጉብኝታቸውን በደስታ አጠናቀው ከሙዚየሙ ቢወጡም፣ አንድ ትልቅ ነገር መዘንጋታቸውን ግን ልባቸው አላወቀም ነበር:: 47 ሺህ የኢትዮጵያ ብር የያዘ ቦርሳ! በዚያው ሰዓት በሙዚየሙ የትኬት ሽያጭ መስኮት ላይ ወ/ሮ ጌራወርቅ አሰፋ በስራዋ ላይ ነበረች:: ለሥራዋ ካላት ጥልቅ ፍቅር ባሻገር፣ የደንበኞችን ደህንነት መጠበቅ የቀዳሚነት ተግባሯ ነው:: በድንገት ያንን ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ስትመለከት፣ ቅንጣት ታህል ሳታመነታና የራስዋን ጥቅም ሳታስቀድም፣ ጉዳዩን ለባልደረቦቿ ጭምር ገልፃ ብሩን በጥንቃቄ ጠብቃ ማቆየትን መረጠች:: ከአራት ሰዓታት ረጅም ጥበቃ በኋላ፣ ሶንግ ጀንግ የጠፋበትን



ገንዘብ አስታውሶ በድንጋጤና በተስፋ መቁረጥ ስሜት ወደ ሙዚየሙ ተመለሰ:: "ገንዘቤን አገኝ ይሆን?" እያለ በጥርጣሬ ቢመጣም፣ የጠበቀው ግን ከጠበቀው በላይ ነበር:: የታማኟ ባለሙያ እጅ የጠፋውን ገንዘብ አንድም ሳንቲም ሳይጎድል አስረከበችው! በወቅቱ ብሩን ሳስረክበው ከሱ በላይ ደስተኛ ነበርኩ፣ ትልቅ ሸክም የተገላገልኩ ያክል እፎይታ ማግኘቷን ነው ወ/ሮ ጌራወርቅ ለኤኤምኤን ዲጂታል ሚዲያ የተናገራለችው፡ ፡ በኢትዮጵያውያን ቅንነት ልቡ የተነካው ሶንግ ጀንግ፣ ያን የማይረሳ ቀን በራሱ የእጅ ጽሁፍ አድናቆቱን እና የወ/ሮ ጌራወርቅን ታማኝነት አስፍሮታል:: ይህ አጋጣሚ ለሁላችንም፣ በተለይም በአገልግሎት ዘርፍ ላለን ባለሙያዎች ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፤ ምክኒያቱም በእኔ ውስጥ ሃገሬ አለች፤ ተቋሜ የሃገር ምልክት ነው ስትል ወ/ሮ ጌራ ወርቅ ገልፃለች::"ታማኝነት የሀገር ገጽታ ነው!" ወ/ሮ ጌራወርቅ ያሳየችው ይህ ድርጊት የእሷን ማንነት ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍና የኢትዮጵያውያንን እንግዳ ተቀባይነት በዓለም ፊት ከፍ የሚያደርግ ነው:: የኢትዮጵያ ቅርስ ባለስልጣን የብሔራዊ ሙዚየም መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ለዚህች የሥነ-ምግባር አርአያ የምስጋና ደብዳቤ በማበርከት እውቅና እንደሰጣትና በዚህም ደስተኛ መሆኗን ተናግራለች::

# ኪነ-ጥበብ

## ባለመልካም ምግባር

መሰረቱ ጥሩ ጎዳናው ያማረ ፣
ሀቅን የሚፈልግ ለእውነት ያደረ፣
መልካመነት ግብሩ ሁሉን ያከበረ፣
በቃሉ የሚገኝ ታማኝ የከበረ፡፡
ለሁሉ መሰረት፣ ለነጋችን ህይወት፣
ለዛሬ ማንነት፤ ለመሆን ሰውነት ፣
ሚዛናዊ ሆኖ ለመገኘት በውነት፤
ይበጃል ለሰው ለጅ መሆን መልካምነት፡፡
ባለመልካም ምግባር መልካም ነው ተግባሩ
ተግቶ የሚሰራ ታማኝ ለሀገሩ
አርዓያ የሆነ ተምሳሌት በጥሩ
ባለው ልክ አገልጋይ ቅንነት ምግባሩ
መልካም ስነምግባር ...
ብዙ ነው ዝርዝሩ፤ ብዙ ነው ተግባሩ፡፡
መልካም ስነምግባር ለሰው ልጅ ይበጃል፣
ከሰው ከእንስሳቱ ከሁሉ ያወዳጃል፣
መልካሙን ይዘራል፤ መልካሙን ያፈራል፣
መልካሙን ያገኛል ፤ መልካሙንም ያጭዳል፡፡
እናም መልካም እንሁን ፤መልካምን እንዝራ፣
ለሀገር የሚሆን መልካምን እናፍራ፣
ውሸት እንዲጠፋ ፤እውነት እንዲጠራ፣
ሀገሩን የሚወድ ጸብን የሚፈራ፣
ተዋዶ የሚኖር በፍቅር በጋራ፣
ትውልድ ያስፈልጋል...
ስርቆት የሚጠየፍ ሰርቶ የሚኮራ፡፡
ገና በለጋ እድሜ ስርዓት አሲዞን፣
ሰዎችን አክባሪ እናትና አባትን፣
መምህር ጓደኛ ዘመድ ጎረቤትን፣
ባለመልካም ምግባር ትውልድ ከገነባን፣
ይቀየራል ሁሉ እንለወጣለን፣
ሌብነት ይጠፋል ሰላም እንሆናለን፡፡
ሰላም እንዲመጣ ሙስና እንዲጠፋ፣
ሀገር እንዲለወጥ እድገት እንዲሰፋ፣
በመልካምነት ዘር ፍቅር እንዲበቅል፣
ሰላምን አግኝታ ሀገር እፉ እንድትል፣
ሙስና እንዲጠፋ እድገት እንዲቀጥል፣
መሰረት የሆነ ለነገ የሚባል፣
ባለመልካም ምግባር ትውልድ ያስፈልጋል፣
ባለመልካም ምግባር ትውልድ ያስፈልጋል፡፡

ከያብባል አዲስ